በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መጋቢት 7 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

# 65ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት ዛሬ መጋቢት 7 ቀን 2011 ባካሄደው 65ኛ መደበኛ ስብሰባ በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ ያለ የዋስትና መብት ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ዋስትናው የተጠበቀ ዘመናዊ የብድር ስርአት ግለሰቦችና ተቋማት ተንቀሳቃሽ ንብረታቸውን በማስያዝ ስራ ላይ የሚውል አዲስ ካፒታል ማግኘት እንዲችሉና በሂደቱም የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማሳደግና ለማስፋፋት፣ በዋስትና አስይዞ ብድር ማግኘት የሚቻልበትን ስርአት መዘርጋትና የማስፈጸሚያ መንገዱንም ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ በመሆኑና ለዋስትና በተያዘ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በተወዳዳሪ ባለመብቶች የሚነሳ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን የሚያስችል አንድ ወጥና ሁሉንአቀፍ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኂላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//